ደንብ ቁጥር _______ /፪ሺ፲፪

# የኮቪድ ፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኤኮኖሚ ጉዳዩች ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮችምክር ቤት ደንብ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፺፫/፬ (ሀ) እና የኮቪድ ሥርጭትን ለመከላከል፣ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፬(፩) የሚኒስትሮች ምክር ቤት የወረርሽኙ ሥርጭት እያስከተለ ያለውንና ሊያስከትል የሚችለውን ሰብዓዊ፣ማህበራዊ፣ኤኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳቶች ለመቀነስ እና ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን በሚያወጣቸው ደንቦች እንደሚወስን የተደነገገ በመሆኑ፣

የኮቪድ ፲፱ በአገራችን ኤኮኖሚ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ አንቀጽ ፬(፩) በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪" ማስፈፀሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር _______/፪ሺ፲፪ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ትርጓሜ

ለዚህ ደንብ ዓላማ፡-

፩/ "የንግድ ሥራ" ማለት በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱ አንቀጽ ፪(፪) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

፪/ "አዋጅ" ማለት የኮቪድ ሥርጭትን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር እና የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ የወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፫/፪ሺ፲፪ ነው፡፡

፫/ "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብ ሚኒስቴር ነው፡፡

፬/ በአዋጁ የተሰጡ ሌሎች ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብም ተፈፃሚ ይሆናሉ::

## ፫. <u>ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱ አንቀጽ ፳፮(፬) የተደነገገው ቢኖርም ግብር ከፋዮች በ፪ሺ፲፪ የበጀት ዓመት ያጋጠማቸው ኪሣራ ወደሚቀጥለው የግብር ዓመት ሊሸጋገር ይችላል::

## ፬. <u>ታክስን ስለማስታወቅና ስለመክፈል</u>

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፳፮ እና በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር ፫፻፰/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፲ የተደነገገው ቢኖርም ገቢያቸውን በየወሩ አስታውቀው የሚከፍሉ ግብር ከፋዮች በመጋቢት፣ሚያዝያ እና ግንቦት ፪ሺ፲፪ ወራት የሰበሰቡትን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ወለድና ቅጣት ሳይከፍሉ በሰኔ ፪ሺ፲፪ ወር ላይ አስታውቀው ለመክፈል ይችላሉ::

## ፭. <u>ለበጎ አድራጎት ዓላማ የሚደረጉ ስጦታዎች</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፱፻፸፱ አንቀጽ ፳፬ (፪) የተደነገገው ቢኖርም የኮቪድ ፲፱ ሥርጭትን ለመከላከል መንግሥት ባደረገው ጥሪ መሠረት ግብር ከፋዮች የሚያደርጉት ስጦታ የግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ ከግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ ፳ በመቶ (ሀያ በመቶ) ባልበለጠ መጠን ተቀናሽ ሊደረግ ይችላል::

## ፮. <u>የግል የንግድ ድርጅቶች የጡረታ መዋጮ</u>

በግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር ፯፻፲፭/፪ሺ፫ አንቀጽ ፲፩ የተመለከተው ቢኖርም በንግድ ስራ የተሠማራ የግል ድርጅት በመጋቢት፣ በሚያዝያ እና በግንቦት ፪ሺ፲፪ የሰበሰበውን የጡረታ መዋጮ ወለድና ቅጣት ሳይኖርበት በሰኔ ወር ፪ሺ፲፪ ገቢ ለማድረግ ይችላል::

## ፯. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚያግዝ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## ፰. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከሚያዝያ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ጀምሮ አዋጁ በሥራ ላይ ባለበት ጊዜ ተፈፃሚ ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**አብይ አህመድ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

## REGULATION NO.___/2020

## A REGULATION ISSUED TO IMPLEMENT ECONOMIC MEASURES UNDER THE STATE OF EMERGENCY PROCLAMATION ENACTED TO COUNTER AND CONTROL THE SPREAD OF COVID-19 AND MITIGATE ITS IMPACTS

**WHEREAS,** Article 93 (4) (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Article 4(1) of State of Emergency Proclamation No.3/2020 Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19, provide that the Council of Ministers shall stipulate through Regulation it adopts details of the suspension of rights and measures to be taken to counter and mitigate the humanitarian, social, economic and political damages that could be caused by COVID-19;

WHEREAS, it has become necessary to take measures that help mitigate the economic damage that could be caused by COVID-19;

NOW, THEREFORE, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 4(1) of Proclamation No.3/2010.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "State of Emergency Proclamation No. 3/2020 Implementation Council of Ministers Regulation No._____/2020"

### 2. Definitions

For purposes of this Regulation:

1) " Business" shall have the meaning ascribed to it under Article 2(2) of the Income Tax Proclamation No.979/2016.
2) "Proclamation" means the State of Emergency Proclamation No.3/2020 Enacted to Counter and Control the Spread of COVID-19".
3) " Ministry" means the Ministry of Finance.
4) Definitions provided in the Proclamation are applicable to this Regulation

### 3. Loss Carry Forward

Notwithstanding the provisions of Article 26(4) of the Income Tax Proclamation No. 979/2016, if taxpayers have a loss in 2012 (EC) Fiscal Year, shall carry the amount of such loss to the next fiscal year.

## 4. Filing of Tax Return and Payment of Tax

Notwithstanding the provisions of Article 26 of the Value Added Tax Proclamation, No.286/2002 (as amended) and Article 10 of the Turn Over Tax Proclamation No. 308/2002 (as amended), taxpayers who are required to file tax return and pay the tax every month may file the tax return and pay the tax that shall be due in the month of Megabit, Miazia and Ginbot , 2012 (EC) in the month of Sene 2012(EC) without interest and penalty.

## 5. Charitable Donations

Notwithstanding the provisions of Article 24(2) of the Income Tax Proclamation No.979/2016, a taxpayer shall be allowed a deduction in determining the taxable income of the taxpayer for the amount of a donation made in response to a call issued by the Government to mitigate the impact of COVID-19, in an amount not exceeding 20% (twenty per cent) of the taxable income of the tax payer for the year.

## 6. Pension Contributions of Business Organizations

Notwithstanding the provisions of Article 11 of the Private Organizations Employees' Pension Proclamation No. 715/2011, pension contribution of organizations engaged in business due in the month of Megabit, Miazia and Ginbot 2012 (EC) shall be paid in the month of Sene 2012 (EC).

## 7. Power to Issue Directives

The Ministry is hereby empowered to issue directives for the proper implementation of this Regulation.

## 8. Effective Date

This Regulation shall be effective from 24th April 2020, the day it has been adopted by the Council of Ministers, through out the period the Proclamation remains in force.

**Done at Addis Ababa this 24th day of April 2020.**

**ABIY AHMED (PhD)**
**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**



የገንዘብ ሚኒስቴር ሪከርድ ክፍል ትራፊክ 2